# ደም ነው ሥርየቱ

ዐባይ ቢሻው ይጉረፍ በጣና ላይ ነግሶ
አሎሃ ይደፍርስ ተከዜም ደም ለብሶ
ማሂንም አቋሽም ጓንግም ቁልቁል ይፍሰስ ይትመም እያጓራ
መሻገሪያ ይንሳ እስኪያልፍ ክረምቱ በጉልበቱ ይኩራ
ምኑንም ምኑንም እርጥቡን ከደረቅ ያጉዘው ሙላቱ
እንደ አባት አደሩ እንደ ይትባህሉ ዛሬም እንደ ጥንቱ
የጎቤ መልኬም ሞት ደም በደም ይፀዳል ደም ነው ሥርየቱ።

ለጀግና ዕምባ አይረጩም ፀጉርም አይላጩም
ዋይታና ለቅሶ ሙሾ አይደረድሩም ወይም ፊት አይነጩም
እንደ አባት አደሩ እንደ ጎንደር በሃል
ደም ነው ሥርየቱ ደም በደም ይፀዳል።

አለፋ ጣቁሳ ደንቢያና ፎገራ
ጭልጋ ገለድባ ከሽንፋ እስከ ቋራ
ጎዛምን በላያ ከመተከል ፓዌ ከሻግኔ ወንበራ
ከፍኖተ ሰላም ማንኩሳ እንጅባራ
መተማ ሰራቆ ጫቆና አዳኝ አገር
ቆላ ደጋ ዳሞት ቋሪትና አቸፈር
እነሴና ነብሴ ሞጣ ቀራኒዎ ጭስ ዐባይ ባህር ዳር
ነፋስ መውጫ ጋይንት እስቴ ደብረ ታቦር
መልዛ መቀጠዋ ዝዊና ዘሃዬ
ጎጃም ከአባ ኮስትር ጎንደር ከገብርዬ
ከዚያ እስከዚህ ድረስ ሞፈር መቁረጥ ያውቃል
እምቢተኝነቱ ካልተለበለበ መቼ ይታረቃል።

ወልዲያና ሰቆጣ ዳህናና ሳህላ
ዳሆጭና ኮዛ ኪንፋዝ ወይ በገላ
በየዳና አምባራስ ሰሜን ጃናሞራ
ጠገዴና ጠለምት አጅሬ ጃኖራ
ሰራቆና ማሂን ከድሮም ሲፈጠር ወልቃይት ሲሠራ
አርማጭሆና እንቃሽ አይባና ወገራ
አያውቅም ለቅሶ ደም ይረጫል እንጂ እየፈላ አሞቱ
እንደ ቀራኒዎው የይሁዳ ክህደት ሲሆንበት ሞቱ
እንደ አምላኩ ስቅለት ደም በደም ይፀዳል ደም ነው ሥርየቱ።

የካቲት 2009
አብርሃም በየነ